# ትንቢተ ዕንባቆም

**1** ነቢዩ ዕንባቆም የተቀበለው ንግር፤

### *የዕንባቆም ማጕረምረም*

[2]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ለርዳታ እየተጣራሁ፣
አንተ የማትሰማው እስከ መቼ ነው?
“ግፍ በዛ” ብዬ እየጮኽሁ፣
አንተ የማታድነው እስከ መቼ ነው?
[3]ስለ ምን በደልን እንዳይ አደረግኸኝ?
እንዴትስ ግፍ ሲፈጸም ትታገሣለህ?
ጥፋትና ግፍ በፊቴ አለ፤
ጠብና ግጭት በዝቶአል፡፡
[4]ስለዚህ ሕግ ላልቶአል፤
ፍትሕ ድል አይነሣም፤
ፍትሕ ይጣመም ዘንድ፣
ክፉዎች ጻድቃንን ይከባሉ፡፡

### *የእግዚአብሔር መልስ*

[5]“ቢነገራችሁም እንኳ፣
የማታምኑትን እናንተን፣
በዘመናችሁ አንድ ነገር ስለማደርግ፣
እነሆ፤ ሕዝቡን እዩ፤ ተመልከቱም፤
እጅግም ተደነቁ፡፡
[6]የራሳቸው ያልሆኑትን መኖሪያ ስፍራዎች
ለመያዝ፣
ምድርን ሁሉ የሚወሩትን፣
ጨካኝና ፈጣን የሆኑትን፣
ባቢሎናውያንን[ሀ] አስነሣለሁ፡፡
[7]እነርሱም የሚያስፈሩና የሚያስደነግጡ
ናቸው፤
ፍርዳቸውና ክብራቸው፣
ከራሳቸው ይወጣል፡፡
[8]ፈረሶቻቸው ከነብር ይልቅ ፈጣኖች፣
ከማታም ተኵላ ይልቅ ጨካኞች ናቸው፡፡
ፈረሰኞቻቸው በፍጥነት ይጋልባሉ፤
ከሩቅ ስፍራም ይመጣሉ፡፡
ነጥቆ ለመብላት እንደሚቸኵል አሞራ
ይበራሉ፤
[9]ሁሉም ለዐመፅ ታጥቀው ይመጣሉ፡፡
ሰራዊታቸው[ለ] እንደ ምድረ በዳ ነፋስ
ወደ ፊት ይገሠግሣል፤
ምርኮኞችንም እንደ አሸዋ ይሰበስባል፡፡
[10]ነገሥታትን ይንቃል፤
በገዦችም ላይ ያፌዛል፤
በምሽግ ሁሉ ላይ ይሥቃል፤
የዐፈር ቍልል ሠርቶም ይይዘዋል፡፡
[11]ከዚያም በኋላ እንደ ነፋስ ዐልፎ
ይሄዳል፤
ጕልበታቸውን አምላካቸው ያደረጉ
በደለኞች ናቸው፡፡

### *የዕንባቆም ዳግመኛ ማጕረምረም*

[12]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከዘላለም ጀምሮ ያለህ
አይደለህምን?
የእኔ አምላክ፣ የእኔ ቅዱስ እኛ አንሞትም፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እንዲፈርዱ ሾመሃቸዋል፤
ዐለት ሆይ፤ ይቀጡ ዘንድ ሥልጣን
ሰጠሃቸው፡፡
[13]ዐይኖችህ ክፉውን እንዳያዩ እጅግ ንጹሓን
ናቸው፤
አንተ በደልን መታገሥ አትችልም፤
ታዲያ፣ አታላዮችን ለምን ትታገሣለህ?
ክፉው ከራሱ ይልቅ ጻድቅ የሆነውን
ሲውጠውስ፣
ለምን ዝም ትላለህ?
[14]አንተ ሰዎችን በባሕር ውስጥ እንዳለ ዓሣ፣
ገዥ እንደሌላቸውም የባሕር ፍጥረታት
አደረግሃቸው፡፡
[15]ክፉ ጠላት ሁሉንም በመንጠቆ ያወጣቸዋል፤
በመረቡ ይይዛቸዋል፤
በአሽክላው ውስጥ ይሰበስባቸዋል፤
በዚህም ይደሰታል፤ ሐሤትም ያደርጋል፡፡
[16]በእነርሱ ተዝናንቶ ይኖራልና፤
ምግቡም ሰብቶአል፡፡
ስለዚህ ለመረቡ ይሠዋል፤
ለአሽክላውም ያጥናል፡፡
[17]ታዲያ መረቡን ባለማቋረጥ መጣል፣
ሕዝቦችንስ ያለ ርኅራኄ መግደል
አለበትን?

**2** በመጠበቂያ ላይ እቆማለሁ፤
በምሽጉ ቅጥር ላይ ወጥቼ
እቈያለሁ፤
ምን እንደሚለኝ፣
ለክርክሩም[ሐ] የምሰጠውን መልስ ለማወቅ
እጠባበቃለሁ፡፡

### የእግዚአብሔር መልስ

[2]*እግዚአብሔርም* እንዲህ ሲል መለሰ፤
“በቀላሉ እንዲነበብ፣
ራእዩን ጻፈው፤
በሰሌዳም ላይ ቅረጸው፡፡
[3]ራእዩ የተወሰነለትን ጊዜ ይጠብቃልና፤
ስለ መጨረሻውም ይናገራል፤
እርሱም አይዋሽም፤
የሚዘገይ ቢመስልም ጠብቀው፤

[ሀ]6 *ከለዳውያን* ማለት ነው፡፡
[ለ]9 የዕብራይስጡ ቃል ትርጕም በትክክል አይታወቅም፡፡
[ሐ]1 ወይም *በተገሠጽሁ ጊዜ የምሰጠውን ምላሽ*

1፥1 ናሆ1፥1
1፥2 መዝ6፥3፤ 13፥12፤22፥12፤ ኤር14፥9ዘካ1፥12
1፥3 ቍ13፤ ኢሳ9፥23፤ መዝ55፥9፤ ኤር20፥8
1፥4 ኢዮ19፥7፤ መዝ119፥126፤ ኢሳ1፥23፤5፥20፤ 29፥21፤ሕዝ9፥9
1፥5 ኢሳ29፥9፤ ሐሥ13፥41
1፥6 ዘዳ28፥49፤ 2ነገ24፥2፤ኤር13፥20 ፤21፥7፤ራእ20፥9
1፥7 ኢሳ18፥7፤ ኤር39፥59
1፥8 ዘፍ49፥27 ኤር4፥13
1፥9 ዕን2፥5
1፥10 2ዜና36፥6፤ ኤር33፥4
1፥11 ኤር4፥1112፤ ዳን4፥30
1፥12 ዘፍ21፥33፤ 49፥24፤ዘፀ33፥22፤ መዝ118፥17፤ ኢሳ10፥6፤31፥1 ፤37፥23
1፥13 ቍ3፤ ኢዮ21፥7፤ መዝ18፥26፤25፥3፤ ሰቆ3፥34፡36
1፥15 ኢዮ18፥8፤ ኢሳ19፥8፤ኤር5፥26፤ 16፥16
1፥16 ኤር44፥8
1፥17 ኢሳ14፥6፤ 19፥8
2፥1 መዝ5፥3፤48፥13 ፤85፥8፤ኢሳ21፥8፤ ሕዝ3፥17
2፥2 ኢሳ30፥8፤ ኤር36፥2፤ሕዝ24፥2፤ ሮሜ4፥24፤ራእ19
2፥3 መዝ27፥14፤ ሕዝ12፥25፤ ዳን8፥17፤11፥27

በርግጥ ይመጣል[ሙ]፤ ከቶም አይዘገይም።
4“እነሆ፤ እርሱ ታብዮአል፤
ምኞቱ ቀና አይደለም፤
ጻድቅ ግን በእምነቱ[ሠ] ይኖራል።
5በርግጥ የወይን ጠጅ አታሎታል፤
ትዕቢተኛ ነው፤ ከቶ አያርፍም፤
እንደ ሲኦል[ረ] ስስታም ነው፤
እንደ ሞት ከቶ አይጠግብም፤
ሕዝቦችን ለራሱ ይሰበስባል፤
ሰዎችንም ሁሉ ማርኮ ይወስዳል።
6“ታዲያ በእንደዚህ ዐይነቱ ሰው ላይ በማፌዝና በመዘበት እንዲህ እያሉ ሁሉም አይሣለቁበትምን?
“የተሰረቀውን ሸቀጥ ለራሱ ለሚያከማች፤
ራሱን በዐመፅ ባለጠጋ ለሚያደርግ
ወዮለት!
ይህ የሚቀጥለውስ እስከ መቼ ነው?”
7ባለ ዕዳ[ሰ] ያደረግሃቸው ድንገት
አይነሡብህምን?
ነቅተውስ አያስደነግጡህምን?
በእጃቸውም ትወድቃለህ።
8አንተ ብዙ ሕዝብ ስለ ዘረፍህ፤
የተረፉት ሕዝቦች ይዘርፉሃል፤
የሰው ደም አፍሰሃልና፤
አገሮችንና ከተሞችን፤ በውስጣቸው
የሚኖሩትን ሁሉ አጥፍተሃል።
9“በተጭበረበረ ትርፍ መኖሪያውን
ለሚገነባ፤
ከጠላት እጅ ለማምለጥ፤
ቤቱን በከፍታ ላይ ለሚሠራ ወዮለት!
10የብዙ ሰዎች ነፍስ እንዲጠፋ አሢረሃል፤
በገዛ ቤትህ ላይ ውርደትን፤ በራስህም
ላይ ጥፋትን አምጥተሃል።
11ድንጋይ ከቅጥሩ ውስጥ ይጮኻል፤
ከዕንጨት የተሠሩ ተሸካሚዎችም
ይመልሱለታል።
12“ከተማን ደም በማፍሰስ ለሚሠራ፤
በወንጀልም ለሚመሠርታት ወዮለት።
13ሰዎች ለእሳት ማገዶ እንዲሆን እንዲለፉ፤
ሕዝቦችም በከንቱ እንዲደክሙ፤
እግዚአብሔር ጸባኦት ወስኖ የለምን?
14ውሃ ባሕርን እንደሚሸፍን ሁሉ፤
ምድርም የእግዚአብሔርን ክብር በማወቅ
ትሞላለችና።
15“ኀፍረተ ሥጋቸውን ለማየት፤
ባልንጀሮቹን ለሚያጠጣ፤
እስኪሰክሩም ድረስ ወይን ለሚቀዳ
ላቸው ወዮለት!
16በክብር ፈንታ ዕፍረት ትሞላለህ፤
አሁን ደግሞ ተራው የአንተ ነውና፤

2፥4 ሕዝ18፥9፤ ሮሜ1፥17፤ገላ3፥11፤ ዕብ10፥3738
2፥5 ምሳ20፥1፤ 27፥20፤30፥1516፤ ኢሳ2፥11፤ዕን1፥9
2፥6 ኢሳ14፥4፤ አሞ2፥8
2፥7 ምሳ29፥1
2፥8 ቍ17፤ ኢሳ33፥1፤ ኤር50፥1718፤ ሕዝ39፥10፤ አብ1፥15፤ዘካ2፥89
2፥9 ኢዩ39፥27፤ ኢሳ 10፥14፤ ኤር22፥13፤51፥13
2፥10 ቍ16፤ ኤር26፥19፤ናሆ3፥6
2፥11 ኢሱ24፥27፤ ዘካ5፥4፤ሉቃ19፥40
2፥12 ሕዝ22፥2፤ ሚክ3፥10
2፥13 ኢሳ47፥13፤ 50፥11
2፥14 ዘፀ16፥7፤ ዘኍ14፥21፤ኢሳ11፥9
2፥15 ምሳ23፥20
2፥16 ቍ10፤ ዘሌ10፥9፤መዝ16፥5፤ ኢሳ51፥22፤ሰቆ4፥21፤ ሕዝ 23፥32፡34፤ ሆሴ4፥7
2፥17 ቍ8፤ ኤር50፥15፤51፥35
2፥18 ዘሌ26፥1፤ መሳ10፥14፤ 1ሳሙ 12፥21፤ መዝ115፥45፤ ኢሳ40፥19፤ኤር5፥21 ፤10፥14፤14፥22፤ 1ቆሮ12፥2
2፥19 1ነገ18፥27፤ ኤር10፥4፤ ዳን5፥4፡23፤ ሆሴ4፥12
2፥20 መዝ11፥4፤ ኢሳ41፥1
3፥1 መዝ7 ርእስ
3፥2 ኢዮ26፥14፤ መዝ44፥1፤85፥6፤ 90፥16፤119፥120፤ ኢሳ54፥8፤
3፥3 ዘፍ36፥11፡15፤ ዘኍ10፥12፤መዝ8፥1፤ 48፥10፤ኢሳ31፥1
3፥4 ኢዮ9፥6፤ ኢሳ18፥4
3፥5 ዘሌ26፥25
3፥6 ዘፍ21፥33፤ 49፥26፤ዘፀ19፥18፤ መዝ18፥7፤46፥2፤ 114፥16

ጠጣና ኀፍረተ ሥጋህ ይገለጥ፤
በእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ያለው ጽዋ
ይመለስብሃል፤
ክብርህንም ውርደት ይሸፍነዋል።
17በሊባኖስ ላይ የሠራኸው ግፍ
ያጥለቀልቅሃል፤
እንስሳቱን ማጥፋትህም ያስደነግጥሃል፤
የሰው ደም አፍሰሃልና፤
አገሮችንና ከተሞችን በውስጣቸው
የሚኖሩትንም ሁሉ አጥፍተሃልና።
18“የሰው እጅ የቀረጸው ጣዖት፤
ሐሰትንም የሚናገር ምስል ምን ፋይዳ
አለው?
ሠሪው በገዛ እጁ ሥራ ይታመናልና፤
መናገር የማይችሉ ጣዖታትን
ይሠራል።
19ዕንጨቱን፤ ‘ንቃ!’
ሕይወት የሌለውንም ድንጋይ፤ ‘ተነሣ!’
ለሚል ወዮለት፤
በውኑ ማስተማር ይችላልን?
እነሆ፤ በወርቅና በብር ተለብጦአል፤
እስትንፋስም የለውም።
20እግዚአብሔር ግን በተቀደሰ መቅደሱ አለ፤
ምድር ሁሉ በፊቱ ጸጥ ትበል።”

## የዕንባቆም ጸሎት

3 በዝማሬ የቀረበ የነቢዩ የዕንባቆም ጸሎት፤
በሽግዮኖት[ሸ]

2እግዚአብሔር ሆይ፤ ዝናህን ሰምቻለሁ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ሥራህም አስፈራኝ፤
በእኛ ዘመን አድሳቸው፤
በእኛም ጊዜ እንዲታወቁ አድርግ፤
በመዓት ጊዜ ምሕረትን አስብ።
3እግዚአብሔር ከቴማን፤
ቅዱሱም ከፋራን ተራራ መጣ። ሴላ[ቀ]
ክብሩ ሰማያትን ሸፈነ፤
ውዳሴውም ምድርን ሞላ።
4ጸዳሉ እንደ ፀሓይ ብርሃን ነው፤
ጨረር ከእጁ ወጣ፤
ኀይሉም በዚያ ተሰውሮአል።
5መቅሠፍት በፊቱ ሄደ፤
ቸነፈርም እግር በእግር ተከተለው።
6ቆመ፤ ምድርን አንቀጠቀጠ፤
ተመለከተ፤ ሕዝቦችን አብረከረከ፤
የዘላለም ተራሮች ተፈረካከሱ፤
የጥንት ኰረብቶችም ፈራረሱ፤
መንገዱ ዘላለማዊ ነው።

[ሙ]3 የሚመጣ ሰው እንዳለ የሚያመለክቱ አሉ።
[ሠ]4 *በታማኝነቱ* የሚሉ አሉ።
[ረ]5 *መቃብር* የሚሉ አሉ።
[ሰ]7 ወይም *አበዳሪ* ነው።
[ሸ]1 የሥነ ጽሑፍ ወይም የሙዚቃ ቋንቋ ሳይሆን አይቀርም
[ቀ]3 ትርጕሙ በትክክል የማይታወቅ ቢሆንም የዜማ ቃል ሳይ ሆን አይቀርም

7የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ፣
የምድያምም መኖሪያዎች ሲታወኩ
አየሁ።

8እግዚአብሔር ሆይ፤ በወንዞች ላይ ተቈጣህን?
መዓትህስ በምንጮች ላይ ነበርን?
በፈረሶችህና በድል አድራጊ ሠረገሎችህ፣
በጋለብህ ጊዜ፣
በባሕር ላይ ተቈጥተህ ነበርን?
9ቀስትህን አዘጋጀህ፤
ፍላጻም እንዲመጣልህ አዘዝህ፤
ሴላ
ምድርን በወንዞች ከፈልህ፤
10ተራሮች አዩህ፤ ተጨነቁም፤
የውሃ ሞገድ ዐልፎ ሄደ፤
ቀላዩ ደነፋ፤
ማዕበሉንም ወደ ላይ አነሣ።

11ከሚወረወሩ ፍላጾችህ፣
ከሚያብረቀርቅ የጦርህ ነጸብራቅ የተነሣም፣
ፀሓይና ጨረቃ በቦታቸው ቆሙ።
12በምድር ላይ በመዓት ተመላለስህ፤
ሕዝቦችንም በቍጣ ረገጥሃቸው።
13ሕዝብህን ለመታደግ፣
የቀባኸውንም ለማዳን ወጣህ፤
የክፉትን ምድር መሪ ቀጠቀጥህ፤
ከራስ ጠጕሩ እስከ እግር ጥፍሩም
ዕርቃኑን አስቀረኸው።

14እንደ ዐውሎ ነፋስ ሊበታትነን የመጣውን፣
ምስኪኑን በስውር በመዋጥ
የሚደሰተውን፣
የሰራዊት አለቃ ራስ፣
በገዛ ጦሩ ወጋህ።
15ታላላቅ ውሆችን በመናጥ፣
ባሕሩን በፈረሶችህ ረገጥህ።
16እኔ ሰማሁ፤ ልቤም ደነገጠብኝ፤
ከንፈሬ ከድምፁ የተነሣ ተንቀጠቀጠ፤
ፍርሀት እስከ ዐጥንቴ ዘልቆ ገባ፤
እግሬም ተብረከረከ፤
ሆኖም በሚወረን ሕዝብ ላይ እስኪመጣ
ድረስ፣
የጥፋትን ቀን በትዕግሥት እጠባበቃለሁ።
17ምንም እንኳ የበለስ ዛፍ ባያፈራ፣
ከወይን ተክልም ፍሬ ባይገኝ፣
የወይራም ዛፍ ፍሬ ባይሰጥ፣
ዕርሻዎችም ሰብል ባይሰጡ፣
የበጎች ጕረኖ እንኳ ባዶውን ቢቀር፣
ላሞችም በበረት ውስጥ ባይገኙ፣
18እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤
በድነቴ አምላክ ሐሤት አደርጋለሁ።

19ጌታ እግዚአብሔር ኀይሌ ነው፤
እግሮቼን እንደ ዋላ እግሮች ያደርጋል፤
በከፍታዎችም ላይ ያስሄደኛል።

ለመዘምራን አለቃ፣ በባለ አውታር
መሣሪያዎቼ የተዘመረ መዝሙር።

3÷7 ዘፍ25÷2፤ ዘፀ15÷14፤ዘኍ25÷15 ፤መሳ7÷2425
3÷8 ዘፀ7÷20፤ 2ነገ2÷11፤ መዝ68÷17፤77÷16
3÷9 ዘዳ32÷23፤ መዝ7÷1213
3÷10 መዝ77÷16፤ 93÷3፤98÷7
3÷11 ኢሱ10÷13፤ መዝ18÷14፤144÷6፤ ዘካ9÷14
3÷12 ኢሳ41÷15
3÷13 ዘፀ13÷21፤ 2ሳሙ23÷1፤ መዝ20÷6፤28÷8፤ 68÷21፤110÷6
3÷14 መሳ7÷22 መዝ64÷25
3÷15 ዘፀ15÷8፤ ኢዮ9÷8
3÷16 ኢዮ4÷14፤ መዝ37÷7
3÷17 ኤር5÷17፤ ኢል1÷1012:18
3÷18 ዘፀ15÷2፤ መዝ97÷12፤ አሳ61÷10፤ ሉቃ1÷47፤ፊል4÷4
3÷19 ዘዳ32÷13፤ 33፤29፤መዝ18÷33፤ 46÷15